የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፷፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 65
ADDIS ABABA 23rd May 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፴፬/፪ሺ፫
የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ............ገጽ ፭ሺ፰፻፸፮

## CONTENTS

Regulation No.234 /2011
Bahir Dar University Re-establishment
Council of Ministers Regulation ..............Page 5876

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፬/፪ሺ፫

**ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር. ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፬/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **መቋቋም**

፩/ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል።

፪/ ዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል ።

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል።

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 234 /2011

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE–ESTABLISHMENT OF THE BAHIR DAR UNIVERSTIY**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5 (1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Bahir Dar University Re-establishment Council of Ministers Regulation No. 234 /2011".

2. **Establishment**

1/ The Bahir Dar University (hereinafter the "University") is hereby re-established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No.210 /2011.

፫. **ዋና ግቢ**

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በባህርዳር ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፬ **የተሻረ ደንብ**

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷/፲፱፻፺፱ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፭. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

3. **Main Campus**

The University shall have its main campus at Bahir Dar and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services .

4. **Repealed Regulation**

The Bahir Dar University Establishment Council of Ministers Regulation No. 60/1999 is hereby repealed.

5. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 23 rd day of May , 2011.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት